# ትምህርት 66

1. የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን በፋሲካ በዓል ለመያዝ ያልፈለጉት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስን በፋሲካው በዓል ሰሞን ከያዙት ሕዝቡ ዐመፅ ያስነሳል የሚል ፍርሃት ስለ ነበራቸው ነው።

2. ይሁዳ በኃጢአት መወለዱንና የኢየሱስ አዳኝነት የሚያስፈልገው መሆኑን ያውቅ ነበር?

ሀ- አያወቅም።

3. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ የመራው ማን ነበር?

ሀ- ሰይጣን።

4. ሰይጣን ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ የፈለገው ለምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስን ስለሚጠላ።

5. ሰይጣን ኢየሱስን የሚጠላው ለምንድነው?

ሀ- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ።

ለ- ኢየሱስ እውነትን ስለሚናገር።

6. ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉ የፈለገው ለምንድነው?

ሀ- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት የፈለገው ኢየሱስ እኛን እንዳያድነን ስለፈለገ ነው።

ለ- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት የፈለገው ኢየሱስ የኃጢአትንና የሞትን ኃይል እንዳያጠፋ ነው።

ሐ- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉ የፈለገው ኢየሱስ የራሱ የሰይጣንን ሀይል እንዳያጠፋ ነው። [65፡40]

7. ነቢያት አዳኙን ማን አሳልፎ እንደሚሰጥ ተናገሩ?
ሀ- የቅርብ ወዳጁ።

8. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው በምን ያህል ገንዘብ ነበር?
ሀ- በሰላሳ ብር።

9. ኢየሱስ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው እንዴት አወቀ?
ሀ- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ያውቃል።
ለ- ኢየሱስ የማያውቀው ምንም ነገር የለም።

10. እንጀራው የኢየሱስ ሥጋ ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው?
ሀ- እንጀራው እንደ ተቆረሰ ሁሉ የኢየሱስም ሥጋ በክፉ ሰዎች እጅ የሚቆረስ መሆኑ።

11. ወይኑ የኢየሱስ ደም ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው?
ሀ- ወይን ለመጠጣት እንደሚቀዳ ሁሉ የኢየሱስ ደምም የሚፈስ በመሆኑ።

12. ኢየሱስ ደሙ የሚፈሰው ለማን ነው አለ?
ሀ- ኢየሱስ ደሙ ሚፈስሰው ለብዙ ሰዎች ነው አለ።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ኢየሩሳሌምን ከለቀቁ በኋላ በደብረዘይት ተራራ ወደሚገኘው የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ሄዱ።

ማርቆስ 14፡32-36

32- ከዚህ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ ሄዱ፤ ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን፥ «እኔ ስፀልይ እናንተ እዚህ ቈዩ»አላቸው።

33-ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስንም ይዞ ሄደ፤ እጅግ ያዝን ይጨነቅ ነበር።

34-ደግሞም «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ እዚሁ ሁኑና ነቅታችሁ ጠብቁ»አላቸው።

35-ጥቂት እልፍ ብሎም በምድር ላይ በመውደቅ ቢቻል ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ ጸለየና፡-

36-«አባ፤ አባት ሆይ፤ ሁሉ ይቻልሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» አለ።

- በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ኢየሱስ እጅግ ስለ ተጨነቀ መፀለይ ጀመረ።

- ኢየሱስ እጅግ የተጨነቀው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሥቃይ እንደሚደርስበት ስላወቀ ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ ከፊቱ ያለው ሥቃይ ከዚያ በፊት ማንም ሰው ያልቀመሰው እጅግ አሠቃቂ መሆኑን ስላወቀ ነው።

- ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ቢሆንም ፍፁም ሰውም ነው።

- ለኢየሱስ በፊቱ የነበረው አስፈሪ ሥቃይ መጋፈጥ እጅግ አስቸጋሪ ነበር።

## ማርቆስ 14፡37-42

37-ተመልሶም ሲመጣ ደቀመዛሙርቱን ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም እንዲህ አለው፥ «ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን? አንድ ሰአት ነቅተህ መጠበቅ አቃተህ?

38-ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ፤ ጸልዩም፤ መንፈስ ዝግጁ ነው ሥጋ ግን ደካማ ነው።»

39- እንደገናም ሄዶ መጀመሪያ የጸለየውን ደግሞ ጸለየው።

40- ዳግመኛ ሲመለስ ዐይናቸው እንቅልፍ ከብዶት ተኝተው አገኛቸው፤ የሚመልሱለትንም አያውቁም ነበር።

41- ሦስተኛም ጊዜ መጥቶ እንዲህ አላቸው፤ «አሁንም እንደ ተኛችሁና እንዳረፋችሁ ናችሁ? ይበቃል! ሰዓቲቱ ደርሳለች፤ እነሆ፤ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።

42- ተነሡ እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝ መጥቷል።»

- ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ጸሎቱን እንደጨረሰ ብዙ ሰዎች ሰይፍና ዱላ ይዘው መጡ።

ማርቆስ 14፡43-46

43- ወዲያውኑም እየተናገረ ሳለ ከዓስራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ። አብረውት ሰይፍና ዱላ የያዙ፥ ከካህናት አለቆች፥ ከጻሓፍትና ከሽማግሌዎች የተላኩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።

44- አሳልፎ የሚሰጠውም፥ «እኔ የምስመውን እርሱን ነውና ያዙት፤ ተጠንቅቃችሁ ውሰዱት» በማለት አስቀድሞ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር።

45-እንደደረሰም ወዲያው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ «መምህር ሆይ!» ብሎ ሳመው።

46-ሰዎቹም ኢየሱስን ያዙት፤ አሠሩትም።

- ኢየሱስን ለመያዝ ሰይፍና ዱላ ይዘው የመጡትን ሰዎች ይመራ የነበረው ማን ነበር።

- ይሁዳ።

- ይሁዳና ብዙ ሕዝብ የመጣው ለምን ነበር?

- ኢየሱስን ለመያዝ።

- ይሁዳ ኢየሱስን እንዲያስይዝ የመራው ማን ነበር?

- ሰይጣን።

- በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን ማንን እየመራ ነው?

- ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መስራታቸውን የማያምኑትን ሰዎች ሁሉ እየመራ ነው።

- እግዚአብሔር ስለኃጢአታቸው እንደማይቀጣቸው
የማያምኑት ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

- እግዚአብሔር ስለ መልካም ስራቸው እንደሚቀበላቸው
የማያምኑ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

- ራሳቸውን ማዳን እንደሚችሉ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

- የእግዚአብሔርን ቃል መስማት የማይፈልጉ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

- ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ማመን የማይፈልጉ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው እንዴት ነበር?
- በመሳም።

- ይሁዳ ኢየሱስን እንደሳመው ከይሁዳ ጋር የመጡት ሰዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት።

ማርቆስ 14፡47-49

47- በአቅራቢያው ቆመው ከነበሩት አንዱ ሰይፉን መዝዞ የሊቀካህናቱን አገልጋይ ጆሮ ቆረጠ።

48- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እንደ ወንበዴ በሰይፍና በቈመጥ ልትይዙኝ መጣችሁን?

49- በየዕለቱም በቤተመቅደስ እያስተማርኩ ከእናንተ ጋር ስኖር አልያዛችሁኝም፤ መጻሕፍት ይፈፀሙ ዘንድ ይህ ሆነ»

- ኢየሱስ "መጻሕፍት ይፈፀሙ ዘንድ" ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ከብዙ ዘመናት በፊት በነቢያቱ አማካኝነት በአዳኙ ላይ ስለሚሆነው ነገር የተናገረው ተፈፀመ ማለቱ ነበር።

ማርቆስ 14፡50

50- በዚህ ጊዜ [ሁሉም ደቀመዛሙርቱ] ትተውት ሸሹ።

- የኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ የሸሹት ለምንድን ነው?

- ደቀመዛሙርቱ የሸሹት ስለ ፈሩና ኢየሱስ የተያዘበትን ምክንያት ስላልተረዱ ነው።

- ደቀመዛሙርቱ ያልተረዱት ነገር ምን ነበር?

- ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ከተያዘና ከተገደለ በኋላ እንዴት አዳኝ መሆን እንደሚችል አልተረዱም።

- ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ከሞተ በኋላ እነርሱን ማዳን የሚሚችለው እንዴት እንደሆነ አልተረዱም።

- ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ወዴት ወሰዱት?

ማርቆስ 14፡53-54

53- ኢየሱስንም ወደ ሊቀካህናቱ ወሰዱት። በዚያም የካህናት አለቆች፥ ሽማግሌዎችና ጸሓፍት ሁሉ ተሰበሰቡ።
54- ጴጥሮስም ከሩቅ እየተከተለው እስከ ሊቀካህናቱ ግቢ ዘለቀ፤ በዚያም ተቀምጦ ከሎሌዎቹ ጋር እሳት ይሞቅ ነበር።

- ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ወደ ሊቀካህናቱ ወሰዱት።

- ጴጥሮስ በርቀት ተከተለው፤ ይሁን እንጂ እርሱም እንዳይያዝና እንዳይገደል ፈርቶ ነበር።

- ሰዎቹ ኢየሱስን ወደ ሊቀካህናቱ እንዳመጡት የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች በሙሉ በኢየሱስ ላይ ለመፍረድ ተሰበሰቡ።

ማርቆስ 14፡55

55- የካህናት አለቆችና ሸንጎው በሙሉ ኢየሱስን ለመግደል ምስክር ፈለጉ፤ ነገር ግን ማግኘት አልቻሉም።

- የአይሁድ መሪዎች እንዴት በኢየሱስ ላይ አንድም ስህተት አላገኙም?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ምንም ስህተት ስላልሠራ።

- ምክንያቱም ኢየሱስ ምንም ኃጢአት ስላልሠራ።

- አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ላይ መስክረውበታል፤ ይሁን እንጂ ምስክርነታቸው ውሸት ነበር።

ማርቆስ 14፡56-59

56- ብዙዎች በሐሰት ቢመሰክሩም ቃላቸው አንድ ሊሆን አልቻለም።

57- አንዳንዶቹም ተነስተው እንዲህ ሲሉ በሐሰት መሰከሩበት።

58- ይህ፥ የሰው እጅ የሠራውን ቤተመቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ሌላ የሰው እጅ ያልሰራውን እሰራለሁ» ሲል ሰምተነዋል።

59- ይህም ሆኖ፥ እንኳን ምስክርነታቸው አንድ አልሆነም።

- ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ላይ ምንም ስህተት ሊያገኙበት አልቻሉም።

- እግዚአብሔር ከብዙ ዘመናት በፊት በነቢዩ አማካኝነት በተናገረው መሰረት በአዳኙ ላይ ብዙ የሐሰት ምስክሮች መሰከሩበት።

- ከዚያ ሊቀካህናቱ ተነስቶ ኢየሱስን አናገረው።

ማርቆስ 14፡60-62

60- ሊቀካህናቱም ተነስቶ በፊታቸው በመቆም፥ «እነዚህ በአንተ ላይ የሚመሰክሩት ምንድነው? ለምን አትመልስም» በማለት ኢየሱስን ጠየቀው።

61- ኢየሱስ ግን ዝም አለ፤ ምንም መልስ አልሰጠም። ሊቀካህናቱም እንደገና የቡሩኩ ልጅ፥ ክርስቶስ አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው።

62- ኢየሱስም፥ «አዎ ነኝ፤ የሰው ልጅ በኀያሉ ቀኝ ሲቀመጥ፥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ» አለ።

- ሰዎች በእርሱ ላይ በውሸት ቢመሰክሩበትም ኢየሱስ ምንም መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ።

- ኢየሱስ ምንም መልስ ያልሰጠው ለምንድን ነው?

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ እርሱን እንደሚመራው ስለሚያውቅ ነው።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ በእርሱ ላይ የሚፈጸመውን ነገር ሁሉ እንደሚቆጣጠር ስለሚያውቅ ነው።

- ሊቀካህናቱ ኢየሱስን “የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን?” ብሎ ሲጠይቀው ኢየሱስ ምን መለሰለት?

- ኢየሱስ «አዎ ነኝ» ብሎ መለሰለት።

- እንዲሁም ኢየሱስ «የሰው ልጅ በኀያሉ ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ» አለ።

- ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር ሲመጣ አዳኝ አምላክ ሆኖ ሰዎችን ለማዳን መጣ።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣ ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ ያየዋል።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ሰው ሁሉ ያያል።

- ሊቀካህናቱ የኢየሱስን ንግግር ሲሰማ ምን አደረገ?

ማርቆስ 14፡63-64

63- ሊቀካህናቱ ልብሱን ቀደደና፥ እንዲህ አለ፤ «ሌላ ምን ምስክር ያስፈልገናል?
64- ስድቡን ሰምታችኃል፤ ታዲያ፥ ምን ይመስላችኋል?» እርሱም ሞት ይገባዋል በማለት በአንድ ቃል ፈረዱበት።

- ሊቀካህናቱ ልብሱን የቀደደው ለምን ነበር?

- አይሁዶች እጅግ ሲቆጡ ወይም ሲጨነቁ ልብሳቸውን መቅደድ ልማዳቸው ነበር።

- ሊቀካህናቱ በኢየሱስ ንግግር እጅግ ስለ ተናደደ ልብሱን ቀደደ።

- ሊቀካህናቱ በኢየሱስ የተናደደው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ነኝ ስላለ ነው።

- ሊቀካህናቱ ኢየሱስ መገደል አለበት ያለው ለምን ነበር?

- ሊቀካህናቱ ኢየሱስ መገደል አለበት ያለው እግዚአብሔርን ሰድቦአል ብሎ ነው።

- ኢየሱስ አግዚአብሔርን ሰድቦአል?

- አልሰደበም።

- ኢየሱስ እኔ አምላክ ነኝ ብቻ ነው ያለው።

ማርቆስ 14፥65

65- በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ ይተፉበት ጀመር፤ ዐይኑንም ሸፍነው በጡጫ እየመቱት፥ «እስቲ ትንቢት ተናገር!» ይሉት ነበር። ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።

- እግዚአብሔር ከብዙ ዘመናት በፊት በነቢያቱ አማካኝነት አዳኙ እንድሚመታ እንደሚተፋበትም ተናግሮ ነበር።

- ሊቀካህናቱና የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ እንዲሞት ፈረዱት።